# ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ

Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity

efdpu@aol.com www. Finote.org

ፕሮግራም፡- ረቡዕና እሁድ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት እስከ ሶሰት ሰዓት በ 13 ሜትር ባንድ

**Program**: Wednesday and Sunday 8:00PM- 9:00 PM on 25 meter band.


## ዜና ዘገባ

**ሰኔ 18 ቀን 2003 ዓ.ም**

**የወያኔ ስራ አስፈጻሚ ድንገተኛና አስቸኩዋይ ዝግ ስብሰባ አደረገ፤**

**የወያኔ አባል ያልሆኑ ምሁራኖች ላይ ጥቃት ሊከፈት መሆኑ ተጋለጠ፤**

**የአውራምባ ታይምስ ጋዜጣ ምክትል ዋና አዘጋጅ በወያኔ የደህንነት ክፍል ታፍኖ የደረሰበት ጠፋ፤**

የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሄላሪ ክሊንተን በአዲስ አበባ ሊያደርጉ የነበሩትን ጉብኝት መሰረዝን ተከትሎ የወያኔ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ድንገት አስቸኩዋይ ስብሰባ ማድረጉ ታወቀ።

ሔላሪ ክሊንተን በአፍሪካ ህብረት አዳራሽ ውስጥ ሰኞ ሰኔ 6 ቀን 2003 ዓ.ም ተገኝተው ባደረጉት ንግግር አምባገነን እና ጨፍጫፊ የሆነውን ጋዳፊን አውግዞ ዲፕሎማቶቹንም ከየሀገራችሁ በአስቸኩዋይ አባርሩ በማለት ማስጠንቀቂያ ከመስጠታቸውም በተጨማሪ ዛሬ የአፍሪካ ህዝቦች በተለይ ወጣቶች የዴሞክራሲ በደል እየደረሰባቸው ነው........ ስራ አጥነት ተንሰራፍቶዋል....... የዘረኝነት እና ቡድንተኝነት ተስፋፍቶዋል......ስለዚህ በአስቸኩዋይ ሊስተካከል ይገባል ብለው ማስጠንቀቂያ በሰጡበት በጥቂት ቀናተ ውስጥ እነ መለስ ዜናዊ የስራ አስፈጻሚውን አስቸኩዋይ ስብሰባ መጥራታቸው አነጋጋሪ ሆኗል።

የወያኔ ስራ አስፈጻሚ ቅዳሜ ሰኔ 11 ቀን 2003 ዓ.ም ባደረገው ዝግ ስብሰባ ላይ ተላላኪዎችና ጋዜጠኞች ጭምር እንዳይገቡ ለግማሽ ቀን ተከልክለው የነበረ ሲሆን በተደረገው በዚሁ ዝግ ስብሰባ ክሊንተን በተናገሩት ጠንከራ ሀሳብ ላይና በሌሎቸ ጉዳዮች ላይ ሳይወያዩ እንዳልቀሩ ይገመታል። የአፍሪካ መሪዎች ተላላኪ የሆነው መለስ ዜናዊ በበኩሉ ስልጣኑን ለብቻው ጠቅልሎ ህግ

አውጭነቱን.....እቅድ መንደፉን.....ፕሮጀክት ቀረፃውን...የጦር ኃይሉን በበላይነት በመምራት......የጸረ ሙስና እና የፌዴራል ፖሊስ የበላይ ተቆጣጣሪነት ስልጣኑን በመያዝ ሀገሪቱን እንዳሻው እየተጫቻወተባት ከመሆኑም በተጨማሪ ከዚህ አልፎ ተርፎ የአፍሪካ መሪዎች ለቻይና እንዲያጎበድዱ ከፍተኛ ስራ እየሰራ መሆኑን ግልጥ ሲሆን ከዚህ ተጻራሪ የሆነው የክሊንተን ንግግር እንዳላስደሰተው ግልፅ ነው::

ይህ በእንዲህ እንዳለ እሁድ ሰኔ 12 ቀን 2003 ዓ.ም የአውራምባ ታይምስ ጋዜጣ ምክትል ዋና አዘጋጅ ውብሸት ታዬ በፌዴራል ፖሊስ ከመኖሪያ ቤቱ ታፍኖ ተወስዶ የደረሰበት አለመታወቁ ተገለፀ:::

እሁድ ከቀኑ 9 ሰዓት ላይ ሲሆን ከ30 በላይ የሆኑ የፌዴራል ፖሊሶች እና ሁለት ሲቪል የለበሱ የደህንነት አባሎች በፓትሮል መኪና ከመኖሪያ ቤቱ አፍነው ከመውሰዳቸውም በተጨማሪ መኖሪያ ቤቱን በርብረው የግል ዶኩሜንቶቹን.... ሲዲዎችን.... የቲፕ ክሮችን እና የተለያዩ የግሉ የሆኑ ቁሳቁሶቹን ዘርፈው መውሰዳቸውም ታውቆዋል::

ጋዜጠኛ ውብሸት ታዬ በፌዴራል ፖሊስ ትፈለጋለህ ተብሎ ከመኖሪያ ቤቱ ተወስዶ እስከ ዛሬ ድረስ የት እንደደረሰ ያልታወቀ ሲሆን ቤተሰቦቹ በፍለጋ እላይ ታች እያሉ እየማሰኑ እንደሚገኙም የደረሰን ጥቆማ አጋልጦዋል::

የውብሸት ታዬን ታፍኖ መወሰዱን አስመልክቶ የአውራምባ ታይምስ ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል አስቸኩዋይ መግለጫ ያወጣ ሲሆን በዚሁ ባወጣው መግለጫ ላይ ጋዜጠኛው የደረሰበት ያለመታወቁን ገልፆዋል::

የአውራምባ ታይምስ ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል ባወጣው መግለጫ ላይ እንዳለው ከሆነ ጋዜጠኛ ውብሸት ታዬ የታሰረበትን ምክንያት እንዲገለፅለትና የት እንዳለ እንዲነገረው ለሚመለከተው የወያኔ የደህንነት እና ጸጥታ ቢሮ ጥያቄ ያቀረበ ቢሆንም አጥጋቢ ምላሽ እንዳልተሰጠው ገልፆ ጋዜጠኛ ውብሸት የታሰረው ከጋዜጣው ጋር በተያያዘ አይደለም ተብሎ ምላሽ እንደተሰጠው ገልፆዋል::

ጋዜጠኛ ውብሸት ታዬ በጋዜጣው ላይ በሚያቀርባቸው ወያኔን የሚተቹ ፅሁፎች ከዚህ ቀደም በተደጋጋሚ ግዜ ማዕከላዊ እስር ቤት እየታሰረ የተፈታ ከመሆኑም በላይ በወያኔ ከፍተኛ የደህንነት ሰዎች የመጨረሻ ማስጠንቀቂያ የተሰጠው መሆኑን የገለፁት ለቤተሰቦቹ ቅርበት ያላቸው ወገኖች አሁንም ባለፈው ሳምንት ቅዳሜ ሰኔ 11 ቀን 2003 ዓ.ም ታትሞ ለንባብ በበቃው የአውራምባ ጋዜጣ ላይ «የብተና ፖለቲካ የወለደው አዲስ ምእራፍ» በሚል ወያኔ የህዝብ ድጋፍ እንደሌለውና የተቃዋሚ ፓርቲዎችን እንዴት እየበተነ እንደመጣ ከ1997 ዓ.ም ጀምሮ ያለውን ተጨባጭ እውነታ በማስረጃ እያጣቀሰ በመግለፁ በመበሳጨታቸው የተነሳ ጋዜጠኛውን ለእስራት እንዳበቃው እነዚሁ ለቤተሰቦቹ ቅርበት ያላቸው ወገኖች ገልፀዋል::

በአሁኑ ሰዓት በጣት የሚቆጠሩ የነፃው ፕሬስ ጋዜጠኞች ብቻ ለህዝብ እውነተኛ ወሬ በማቅረብ ላይ የሚገኙ ቢሆንም ወያኔ በሚፈጽምባቸው ግፍና መከራ ምክንያት እየተመናመኑ ከግዜ ወደ ግዜ ቁጥራቸው እያነሰ ሲሆን ከነዚህ መሀከል አንዱ ውብሸት መሆኑን የጠቀሰው የደረሰን ዘገባ በቅርቡ በፀደቀው የሽብርተኝነት ህግ ስም ጋዜጠኞችን እና ሌሎችንም ዜጎች ድንገት እያፈኑ እየሰወሩ በመሆኑ ለወደፊቱ እጅግ  አስደንጋጭ እና አስፈሪ ሁኔታ በመፈጠሩ ሁሉም ዜጋ  ስጋት ውስጥ ሊወድቅ ችሎዋል::

ከዚህ በፊት በየሳምንቱ ቅዳሜ እየታተመ የሚሰራጨው አዲስ ነገር ጋዜጣ አዘጋጆች በሽብር ወንጀል ሊከሰሱ በዝግጅት ላይ እንደነበሩ ጥቆማ ስለደረሳቸው ሁሉም ከሀገር ጠፍተው ያመለጡ ሲሆን ወያኔ በሀገሪቱ አንድ ብቸኛ ተወዳዳሪ የሌለው አምባገነን ፓርቲ ሆኖ ለመቀጠል እያደረገ ባለው መሰረት 2002 ምርጫን  ሙሉ ለሙሉ የተቆጣጠረው ከመሆኑም በላይ አንድ ለአምስት በሚሉት አደረጃጀት ሁሉንም ዜጎች አባል ማድረግ ባወጣው ግዴታ ያልታቀፈና ያልተሳተፈ ሁሉ በሽብርተኝነት እየተወነጀለ ለእስር እንደሚዳረግ  ሲነገር የነበረ ቢሆንም አሁን ግን ተግባራዊ ማድረጉ ታውቆዋል::

በሌላ ዜና የወያኔ ቡድን በየዓመቱ ከፍተኛ እድገት አስመዘገብኩኝ እያለ እየለፈፈ ባለበት በአሁኑ ወቅት በመላ ሀገሪቱ የኑሮ ውድነቱ እያሻቀበ እንደሚገኝ ከተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች የሚደርሱን ጥቆማዎች ገለፁ::

ከዚህ ቀደም በኩንታል አንድ ሺህ ብር ሲሸጥ የነበረው ጤፍ ዛሬ ከ1300 ብር በላይ የተሰቀለ ሲሆን .....ዘይት በሊትር ከ25 እስከ 30 ሲሸጥ የነበረው በአሁኑ ሰዓት እስከ 70 ብር መሸጥ የተጀመረ በመሆኑ ህዝቡ ለከፍተኛ ችግር ከመዳረጉም በተጨማሪ ከፍተኛ ስጋት ውድ መውደቁን የደረሰን ጥቆማ  ገልፆዋል::

የህዝቡ የኑሮው ደረጃ ከዕለት ወደ ዕለት እያሽቆለቆለ ከመሆኑም በላይ የዋጋ ግሽበቱ እጅግ ፈጣን በሆነ ሁኔታ በመሄዱ አሳሳቢ የሆነ ደረጃ ላይ መድሱረንና ህዝቡ እጅግ ለከፋ የኑሮ ውድነት እንደተዳረገ  የደረሰን ጥቆማ ገልፆዋል::

በቅርቡ የአለም ምግብ ድርጅት ባወጣው ዓመታዊ ሪፖርቱ በአሁኑ ሰዓት ያለው የዋጋ ግሽበት እጅግ ፈጣን እና አሳሳቢ ደረጃ ላይ ደርሶዋል ሲል ያጋለጠ ሲሆን የምግብ ግሽበቱ 40 ከመቶ በላይ መናሩን ይፋ አድርጎዋል::በሚያዚያ ወር 2003 ዓ.ም የነበረው የዋጋ ግሽበት 23 በመቶ የነበረ ሲሆን በሰኔ ወር 2003 ዓ.ም በአንድ ወር ልዩነት ወደ 40 ከመቶ በላይ ማሻቀቡን በግልጽ አስፍሮዋል::የግንቦት ወር የዋጋ ንረት ካለፈው ዓመት ጋር ሲነፃፀር እጅግ አስደንጋጭ የሆነ ጭማሪ ማሳየቱን ገልፆ ዘይት 99 በመቶ ፍራፍሬ 60 ከመቶ ቅመማቅመም 52 በመቶ ጥራጥሬ 60 በመቶ በላይ ማሻቀባቸውን ጨምሮ ዘርዝሮዋል::

የሀገሪቱ ገንዘብ ምንዛሪ  ከግዜ ወደ ግዜ ከማሽቆልቆሉም ጋር በተያያዘ የገንዘቡ  የመግዛት አቅሙ ተዳክሞ ከአፍሪካ ሀገራት ርካሽ የተባለ ገንዘብ ለመሆን የበቃ መሆኑም ታውቆዋል::

ወያኔ የህዝቡን ኑሮ ከመደጎም ይልቅ በህዝቡ እና በሀገሪቱ ስም በበድር እና በእርዳታ የሚያገኘ ውን ገንዘብ ለጦር መሳሪያና የደህንነቱ ማጠናከሪያ እያዋለው በመሆኑ ችግሩ ከመቀረፍ ይልቅ ስር እየሰደደ እና እያደገ ለመሄድም ችሎዋል።

በቅርቡ የህዝብ ድጋፍ አገኝበታለሁ በሚል የዋጋ ማስተካከያ አወጣሁ ብሎ ይፋ ቢያደርግም በቂ ጥናት ሳይደረግበት የተሰራ በመሆኑ እቃዎች ከገበያ እየጠፉ ለእይታ እንኳዋን የናፈቁበት መሆኑን ያስታወሰው ዘገባ ጥቂት ሳይቆይ እንደገና መልሶ የጣለውን ተመን በማንሳቱ ቀድሞ ከነበረው በላይ ዋጋው ሁሉ አሻቅቦ ከህዝቡ መግዛት አቅም በላይ የናረበት ሁኔታ ተፈጥሮ እንዳለም ታውቆዋል።

የወጋ ተመን አወጣሁ ብሎ ባዶ ዲስኩር ሲያሰማ የነበረው የወያኔ ቡድን የደሀውን ክፍል ለመያዝ ተብሎ የተወሰደ እርምጃ ነው ቢልም ወትሮም ደሀው የሚገበያየው በችርቻሮ አንጂ በጅምላ እንዳልነበር እየታወቀ በጅምላ ብቻ እንዲሸጥ ማድረጉ ደሀውን ህዝብ ፈጽሞ የረሳና የዘነጋ ተመን እንደነበርም ነዋሪዎች በምሬት ይገልፃሉ።

ወያኔ ደሀውን ህዝብ በትክክል ቢያውቀው ኖሮ ይህን አይፈጽምም ነበር ያሉት ነዋሪዎቹ ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ደሀ አቅም ስለሌለው አንድ ሊትር ዘይት ወይም አንድ ኪሎ ስኩዋር አይገዛም ። ባገኘው አጋጣሚ ዘይትም ሆነ ስኩዋር በችርቻሮ የ25 ሳንቲምና የ50 ሳንቲም እያለ ነበር ዛሬ ግን የተደላደለ ኑሮ እንደሚኖር ህዝብ ከ10 ሊትር በታች እንዳይሸጥ አድርጎ ተመን አወጣሁ ማለቱ በህዝቡ ላይ እየተሳለቀ እና እየቀለደ አለበለዚያ የወያኔ ሰዎች ብቻ እንዲጠቀሙ ያደረገ ስራ መሆኑን ያመላከተ ነው ሲሉም በብስጭት እየተናገሩ ናቸው።

የወያኔ ቡድን ፈጽሞ ደሀውን ህዝብ አያውቀውም ቢያውቀው ኖሮ እንዲህ ያለ የገበያ ምስቅልቅል አይፈጥርም ነበር ያሉት የአዲስ አበባ ነዋሪዎች ዛሬ የምንፈልጋቸውን እቃዎች ለመግዛት ሳይሆን ለማየት እንኳዋን ተቸግረን ነው ያለነው ሲሉ እጅግ ሆድ በባሰ አገላለፅ እየተናገሩ ይገኛሉ።

ባለፈው ባወጣው የዋጋ ተመን ላይ መሳሳቱን ከመግለፅ ይልቅ ጣቱን ወደ ሌላ እየቀሰረ በስህተት ላይ ስህተት እየፈጸመ ከመሆኑም በላይ አሁንም ሌሎቹን ወንጅሎ የፍየል ወጠጤን ሊዘፍን ሲዳክር ይስተዋላል ሲሉም ነዋሪዎቹ በምሬት ሲናገሩ ተደምጠዋል።

ለህዝቡ ኑሮ መሻሻል ከመጨነቅ ይልቅ የጦር ኃይሉን እያጠናከረ የስልጣን እድሜውን እያራዘመ የሚገኘው የወያኔ ቡድን በቅርቡም በ2 ቢሊዮን ብር ወጪ ከ200 በላይ ዘመናዊ ታንኮችን ከዩክሬን ገዝቶ ማስገባቱ ህዝቡን ከመናቅ አልፎ ምን ያመጣል የሚል ልበ ድፍን እርምጃ እየወሰደ መሆኑን የሚያሳይ ነው ሲሉም ነዋሪዎቹ በንዴት እየገለፁ ናቸው።